# የመለስ አምልኮን በጨረፍታ
# ገልቱ ወይስ ጀግና?

**ዮናስ** 7/9/12

የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና "መስራች" ተመስገን ደሳለኝ በፍትህ ጋዜጣ አንድ በሉ ዓምድ ስር ሲያስተናግዳቸው የነበሩትን ጽሁፎች (articles) "የመለስ አምልኮ" በማለት በመጽሃፍ መልክ አሳትሞ ለንባብ አብቅቷል፡፡

መጽሃፉን በተመለከተም በርካታ የፍትህ አምደኞች የመጽሃፍ ክለሳ (Book review) የሰሩበት ሲሆን እኔ ደግሞ ከመፅሃፍ ክለሳ ባሻገር ልመለከተው ወደደኩና ተመስገን በሚወደው አማርኛ የመለስ አምልኮን በጨረፍታ ለመቃኘት ብእሬን ከወረቀት አገናኘሁ፡፡ ጨረፍታዬም በመጽሃፉ ማውጫ ላይ የተመለከቱትን 32 ርዕስ ጉዳዮች በጥልቀት የማይዳሰስ ፣ ነገር ግን በ5ቱም ክፍሎች ላይ የሚገኙትንና መታየት አለባቸው ያልኳቸውን መሰረታዊ አጀንዳዎች የሚያነሳ ነው፡፡

ስለሆነም ይህ የመጀመሪያ ክፍልና በመጽሃፉ ክፍል አንድ "ሀገራዊ ጉዳዮች" በሚል ርዕስ ስር የቀረቡትን መጣጥፎች የተመለከተ ሲሆን ቀሪዎቹን 4 ክፍሎች ደግሞ በተከታታይ ጨረፍታዬ የምመለስባቸው ይሆናል፡፡ የመጀመሪያ ክፍል ለሆነው የመለስ አምልኮን በጨረፍታ "ገልቱ ወይስ ጀግና" የሚል ርዕስ የሰጠሁት ተመስገን ራሱ በዚሁ ክፍል አንድ መጣጥፉ አንዴ ገልቱ አንዴ ጀግና እየሆነ አልያዝ አልጨበጥ ቢለኝና ቃሎቹንም ያለቦታቸው ሲጠቀምባቸው በማስተዋሌ ነው፡፡

የቀድሞው አዲስ ነገር ጋዜጣ ነገረኛ ሆኖ የምናውቀው ብርሃኑ ደቦጭ አሁን ደግሞ በፍትህ ጋዜጣ ላይ በታሪክ ተመራማሪ ስም የመጽሃፍ ክለሳ (book review) አምደኛ ሆኗል። ይህ "ተመራማሪ" እስካሁን ካስነበበን ክለሳው የተመስገን ደሳለኝ "የመለስ አምልኮ" አንዱ ሲሆን ተመስገንና ስራዎቹ በዚህ "ተመራማሪ "ፍፁም ተወድሰዋል ፣ጀግነዋል፡፡

የነሲሳይ አጌናና ወሰን ሰገድ ገብረ ኪዳን የቃልቲው መንግስትና የቃልቲው ሚስጥሮችን ደግሞ "የረፈደባቸው አይረቤ መጻህፍት" ሲል ውግዘት አውርዶባቸዋል፡፡ የሆነ ሆኖ ከዚህ ቀደም "ፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ" በሚለውና ስድስት ክፍል በዘለቀው መጣጥፌ የዜሮ ድምር ስብስቡን የሃሳብና የሴራ ፖለቲካ ኡደት በተመለከተ ያነሳኋቸው ነጥቦች በመለስ አምልኮም ላይ በግልፅ ተመልክተዋል፡፡

ባለው ነባራዊና ተጨባጩ የሃገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መሰረት ተቃውሞንና ተግዳሮቱን በተመለከተ ባብራራሁበት የፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ መጣጥፌ የሃገሬ ተቃዋሚዎች ምንም አይነት ፕሮግራም ሳይኖራቸውና ህዝብን ማዕከል ሳያደርጉ በሚፈጠሩ

አጀንዳዎች ላይ ሁሉ ጣታቸውን በመስደድ በአቋራጭ ስልጣን ለማገኘት እንደሚፈልጉ በርካታ ማሳያዎች በማቅረብ አረጋግጬም ነበር ።

ይኸውም ስብስቡ እርስ በርሱ መሞጋገስና አንዱ ለአንዱ እንደማጣቀሻ እየቀረበ በሀገሪቷ ላይ የሚያጋጥሙ አሉታዊ ጉዳዮችን በአምደኝነት ስም ማራገብ ዋና ስልታቸው ሲሆን ሲመች ከውጪው ኒዮ ሊበራል ሃይል ጋር በመስራት ሳይመች ደግሞ ይህንኑ ሃይል በመክሰስ እና በማብጠልጠል፤ እንዳየሩ መንቀሳቀስ ልማዳቸው እንደሆነም አብራርቼ ነበር፡፡

ይኸው ጉዳይ ዛሬም የመለስ አምልኮ በተበለው የተመስገን የመጣጥፍ ጥርቅም ላይ መገለጹን ማረጋገጥ  ለፈለገ የመለስ አምልኮን የጀርባ ገጽ አስተያየት መመልከት ብቻ በቂው ነው፡፡ የጀርባ ገጽ አስተያየት ሰጪዎቹ በተለይም ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በህገ ልቦና አንድ ሆነው በተመሳሳይ ቋንቋ ተመስገን ዳሰለኝን እንደ ጥላሁን ግዛው ወይም ዋለልኝ መኮንን ያጀገኑት ሲሆን ነቢዩ ሲራክ የተባለው በመካከለኛው ምስራቅ የቪኦኤ ጋዜጠኛም ሌላውና ተመስገንን "እንዳንተ ያለ ጀግና ከወዴት ይገኛል" ሲል ያሞካሸ የተመስገን "ውድ" ጓደኛ ነው፡፡

የፍትህ አምደኞች በመለስ አምልኮ የጀርባ ገጽ ላይ እደግ ተመንደግ ላሉት ተመስገን ዳሳለኝ ቀጥሎ ሌላ ውዳሴና አምልኮ የቀረበው ደግሞ በዛው የፍትህ ጋዜጣ ሰሞንኛ “ተመራማሪ” ብርሃኑ ደቦጭ ነው፡፡ ይህ አካሄድ በአጠቃላይ የዜሮ ድምር ፖለቲከኞች ስትራቴጂ ስለመሆኑ ደግሞ ከነአለም አቀፍ መገለጫዎቹ በፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ መጣጥፌ ለማሳየት ሞክሬያለሁ፡፡ የስብስቡ መወድስ ያልበቃው የተመስገን አምልኮ በመጽሃፉ መግቢያ ላይም በራሱ በተመስገን በድጋሚ እና ከአምልኮም በላይ በገዘፈ መንገድ ቀርቧል፡፡

ተመስገን መጽሃፉን ለማሳተም ያነሳሳውን ምክንያት በገለጸበት የጥርቅሙ መግቢያ ላይ “. . የህትመት ቁጥሩ እንዲህ ከመብዛቱ በፊት የታተሙትን ጋዜጦች ከወዴት ልናገኝ እንችላለን? የሚለውን የአንባብያን ጥያቄ በምንም መልኩ ማለፍም ሆነ መግፋት አልቻልኩም” ሲል መነሻው አንባቢያን መሆናቸውን እና ታዛዥነቱን (የአንባቢያኑን አክባሪነት) ይገልጻል፡፡ ከዛም ምንም እንኳን እራስን ማወደስ የሀገራችን ባህል ባይሆንም "ጀግናው" ተመስገን ግን “የማይቻለውን ችያለሁ፣ የማይታለፈውን አልፌያለሁ፡፡ ስለምን ቢሉ? መልሱ ስለሀገርና ህዝብ ይሆናል” በማለት እራሱን የማንዴላ እና ጋንዲ አከል ግዝፈት ያጎናጽፋል፡፡ ምንም እንኳ እነማንዴላ እራሳቸውን ማወደስ ገቢራቸው ባይሆንም፡፡

ተመስገን ጋዜጠኛ ሳይሆን አመፅ ቀስቃሽ፣ ጥገኛ ፖለቲከኛ ነው ስል፤ ዓምደኞቹም በተመሳሳይ ለሌላ አላማ የተሰለፉና ስልጣን የጠማቸው ጥማታሞች ናቸው ስል በሞገትኩበት የፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ መጣጥፌ እነ ተመስገን የህዝብ ውክልና የተሰጠው ምክር ቤት በአሸባሪነት ከፈረጃቸው አሸባሪ ድርጅቶች ጋር በአንድነት እንደሚሰለፉ በርካታ ማሳያዎችን ማቅረቤ

ይታወሳል፡፡ ዛሬ ደግሞ ከተነቃበት የነግንቦት ሰባት አሰላለፍ ወጣ ያለው "ጀግናው" ተመስገን የኦነግን ትክክለኛነት በወ/ሮ አልማዝ መኮ በማስታከክ በማቅረብ ገልቱነቱን ያሳየናል፡፡ "ይደረስ ለአጉራ ዘለል ካድሬ" በሚል ርዕስ ያስቀመጠው የመጀመሪያው ክፍል የመጀመሪያ ርዕሰ ጉዳይ "ከመኢሶን እስከ ኦህዴድ ኢህአዴግ፣ ከኦህዴድ እስከ ኦነግ የተጓዙ ብርቱ መንገደኛ ናቸው፡፡" በማለት በስውር አሸባሪ የሆነውን የኦነግ አጀንዳ ሲያስፈጽሙ የነበሩትን አልማዝ መኮ የሚያሞካሸው ተመስገን ደሳለኝ ለአሸባሪው ኦነግ "ብርቱ" ለአባሎቹ ደግሞ "ብርቱ መንገደኞች" የሚል እውቅና እየሰጠ ስለመሆኑ የማይገባው ገልቱ እንጂ ጀግና ሊሆን አይችልም፡፡

በመጽሃፉ መግቢያ ላይ እራሱን ያሞካሸውና ያጀገነው ተመስገን ቀደም ብዬ የጠቀስኩት እና በባህላችን ነውር የሆነው ራስን ማወደስ ትዝ ያለው ገጽ 12 ላይ ሲደርስ ነው፡፡የጎግሉን ኤክስኪዩቲቭ "I am not a <u>hero,</u> ok ? I am a very ordinary person" ንግግር በማውሳት" እኔ ጀግና አይደለሁም" ይለናል፡፡ ይህቺ እኔ ጀግና አይደለሁም የምትለው የተመስገን ይትበሃል ምንጭ የባህል እና የይሉኝታ ሳትሆን አይን ከገባው ጋር ሁሉ እራሱን ማመሳሰል ተፈጥሮአዊ ባህሪው ከሆነው ከራሱ ከተመስገን የፈለቀች አጉል መመጻደቅ ነች፡፡

የጎግሉ ኤክስኪዩቲቭ ይህን ስለማለቱ በድንገት ትዝ ሲለው እኔ ጀግና አይደለሁም የሚለን ተመስገን፤ ታዲያ በመግቢያው ላይ ስለምን ሲል "የማይቻለውን ችያለሁ ፣ የማይታለፈውንም አልፌያለሁ ለህዝብ ስል" በማለት ያደናግረናል፡፡ምክንያቱም የማይቻለውን መቻል የማይታለፈውን ማለፍ የጀግና ተፈጥሮ ስለሆነ። ተራ ቅጥፈት ተራ ቅሸባ ይሏችኋል እንግዲህ ይህ ነው፡፡ የዜሮ ድምር ፖለቲካ አስተሳሰብ ደግሞ መጫረሻው እራሱ ገርፎ እራሱ መጮህ ስለሆነ ተመስገን ገና ብዙ ከራሱ ጋር የተጣላበትን አስተሳሰብ በዚሁ በመለስ አምልኮው የመጣጥፍ ጥርቅሙ እናያለን፡፡

እዚህች ጋር አንድ ነገር ደግሞ ታወሰችኝ (ተመስገን አይን ከገባው ጋር ሁሉ መመሳሰል እንጂ እራሱን መሆን እንደማይችል የሚያረጋግጥልን ጉዳይ ነው ትዝ ያለኝ፡፡) ተመስገን ገዢው ፓርቲን ያሞኘ መስሎት ይሁን አባላቱን ያታለለ ፀብ በሌለበት ስለብሄራዊ እርቅ፣ ቂም በሌለበት ስለቂም በቀል በርካታ ጊዜ መፃፉን ሳስታውስ ሰሞንኛ የነበረው እንድ መጣጥፉም ትዝ አለኝ፡፡ ይኸውም ከቴዲ አፍሮ ጥቁር ሰው የክሊፕ ምረቃ ጋር በማያያዝ ስለ አንድነት፣ ስለፍቅርና ይቅር መባባል ሀገራዊ ጠቀሜታ ተመስገን ደሳለኝ ሰብኮን ነበር ።ይህ የተመስገን ስብከት ቴዲን ለመሆን እንደ ቴዲ ለመወደስ ካለው ፍላጎት የመነጨ እንጂ የራሱ የአመለካከት ውጤት እንዳልሆነ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ምንም እንኳ የመለስ አምልኮ የመጣጥፍ ጥርቅም የታታመው ከቴዲ የክሊፕ ምረቃ በኋላ ቢሆንም እና እኔ ያነበብኩት ደግሞ አሁን በመሆኑ የቅደም ተከተል መፋለስ ቢኖርም ተፈጥሮ ነውና በዚሁ የመጣጥፍ ጥርቅም ላይ ተመስገን ስለህዝብ ሳይሆን ስለራሱና መሰሎቹ ስለፍቅር ሳይሆን ስለቂም በቀል የሚኖር ገልቱ መሆኑን የተረዳሁበትን ነጥብ አግኝቻለሁ፡፡ "አጉራ ዘለሉን" ካድሬ ተመስገን እንዲህ ይለዋል፦ "ዛሬ እንዲህ የምትፎክርበት ኋላ ኪስህ ያለው የድርጅትህ መታወቂያ ነገ መወንጀያህ ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር አለብህ" ገጽ13

በድርጅት መታወቂያ የሚፎክር ይኑር ፤አይኑር፤ የሚያስፈራራ ይኑር፤ አይኑር ፍርድ ቤት ባላረጋገጠበት ወይም ገዢው ፓርቲ መግለጫ ባልሰጠበት ሁኔታ ውስጥ የገዢው ፓርቲ አባል መሆንን ከሃጢያት የሚቆጥረው ተመስገን ከወዲሁ ወየውልህ? ሲል የዜሮ ድምሩን ስብስብ የወደፊት ራዕይ ሳያስበው በመተንፈስ ሚስጥር አባካኝ የሆነ ገልቱ ፖለቲከኛ ይሆናል፡፡ “የአጉራ ዘለሉን” ካድሬ ርእሰ ጉዳይ ለመዘጋት ተምታቶበት የሚያምታታውን ተመስገን ማንነት የምታረጋግጥ አንዲት ነገር ላሳያችሁ፡-

በመግቢያው ላይ እራሱን ያጀገነው ተመስገን የጎግሉ ኤክስኪዩቲቭ ትዝ ሲለው እሱን ለመሆን በመፈለግ ብቻ ያለምንም ተያያዥ ምክያት “እኔ ተራ ሰው ነኝ ብሎ መመጻደቁ  የዜሮ ድምር አስተሳሰብ በህሪ ነው ብያችሁ ነበር፡፡ 12ኛው ገጽ ላይ ተራ የነበረው ተመስገን የጎግሉን ኤክስኪዩተቭ እረሳና አቡነ ጳጥሮስ ትዝ ቢሉት ጊዜ መልሶ "ጀገነ" “እኛም እኮ ኢትዮጲያውያን ነን፤ ኢትዮጵያዊ ጀግንነትን ለራስህ ብቻ አታድርገው. . . ምነው ጃል ሌላው ሌላው ቢቀር እንደ አቡነ ጴጥሮስ አይናችን እያየ ስለ እውነት መስክረን ማለፍ ያቅተናል እንዴ. . .” ገጽ 15 እራሱ ገርፎ እራሱ ለሚጮኸው የዜሮ ድምር ስብስብ መገለጫ ከዚህ በላይ ከወዴት ይመጣልን ይሆን? እንጃ የነሱ ነገር ማለቂያ የሌለው ነውና እንቀጥል፡-

“የሀገራዊ ጉዳዮች” ሁለተኛ ርዐሰ ጉዳይ “ኢትዮጵያዊው ማነው?” በሚል የቀረበና የተመስገን የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥነት የተገለጸበት መጣጥፍ ነው፡፡ የተለያዩ ተመራማሪዎችና የምርምር ተቋማት ለሽብርተኝነት አንድና ወጥ የሆነ ትርጉም ባያገኙለትም ብዙዎቹን የሚያስማማ ትርጓሜና መገለጫዎቹ ግን የሉም ማለት አይደለም፡፡ በተለይም የአሜሪካው የምርመራ ቢሮ FBI  ብዙዎቹን የሚያስማማ ትርጓሜ ለሽብርተኝነት ሰጥቶ በስራ ላይ ያዋለ ሲሆን በርካታ ሀገራትም የሽብርተኝነትን ጽንሰ ሃሳብ ከዚሁ የምርመራ ቢሮ FBI በመነሳት ትርጉም ሰጥተው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡

“Terrorism is the unlawful use of force and violence against persons or property to intimidate or coerce a government, the civilian population, or any segment there of, in furtherance of political or social objectives.”

ይህ አለምን የገዛው የሽብርተኝነት ጽንሰ ሃሳብ “ኢትዮጵያዊው ማነው?” በሚለው የተመስገንን መጣጥፍ ላይ ወደ ጎን ተገፍቶ ይገኛል፡፡ ተመስገን የፀረሽብርተኝነት ህጉን ለመቃወምና በዚሁ ተጠርጥረው የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጣቸውን ጓዶቹን ለመታደግ ሲል አውቆ በስህተት አውቆ በድፍረት የማይሆን አመክንዮ ያቀርባል፡፡

“እያልኩ ያለሁት አልቃይዳ ሰላማዊ አረቦችን (ከገገርው ጋር የማይተባበሩትን) እና የአገልግሎት ተቋማትን የጥቃት ኢላማ አድርጎ አያውቅም ነው፡፡ እንዲህ ካደረገማ እሞትለታለሁ የሚለው አላማው አፈርድሜ በላ እንደማለት ነው፡፡”ገጽ 19

በኦነግ ያልበቃው ምስክሩ ተመስገን ለአልቃይዳ በመመስከር እግረ መንገዱን እላዩ ላይ እየመሰከረ የሚገኝ ገልቱ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ከላይ FBI የሰጠውን የሽብርተኝነት ትርጓሜ ተመስገን ሳያውቀው ቀርቶ ሳይሆን አውቆ በድፍረት አዲስ አይነት የሽብርተኝነት ስትራቴጂውን እንደ ገገር ትርጓሜ አስፍሯል፡፡ ይኸውም በመጀመሪያው ርዕሰ ጉዳይ ላይ “ወየውልህ ላለው ካድሬ” የተፈበረከ አዲስ አይነት የሽብርተኝነት ስትራቴጂ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አልቃይዳ ከገገርው ጋር የማይተባበሩትን አይነካም ማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ያገኙት እነ አንዱለምና ጓዶቻቸው ሲያሴሩ የነበሩት መንግስት ላይ እና የገገርው ፓርቲ አካላት ላይ ብቻ ነበር ማለት ነው የሚል ትርጉም ይሰጠናል፡፡

ሌላው ኢትዮጵያዊው ማነው? የሚለው መጣጥፍ በተጨባጭ የሚያረጋግጠው ከገገርው ፖርቲ ውጪ ያሉት ብቻ ናቸው ኢትዮጵያውያን የሚለውን አስተሳሰብ ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነን ተጨማሪ ነገር በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በገጽ 21 የኢዴፓውን ልደቱ አያሌው በተመለከተ በተመስገን የሰፈረው ነጥብ ነው፡፡ ምርጫ 97 ን በማስታወስ ከዜሮ ድምሩ ስብሰብ ራሱን በመነጠል 3ኛ አማራጭ ይዞ የቀረበውን ኤዴፓና መሪውን ልደቱ አያሌው በመኮነን ከገገርው ፓርቲ ጋር ሊያጣብቃቸው ሞክሯል፡፡ ልደቱ አያሌው ኢህአዴግ ሆኑም አልሆኑ ፣ ምንም የመሆን መብታቸው የተጠበቀ ነው ።በነተመስገን የሌላ ጊዜ ውትወታ መሰረት የፈለጋቸውን መሆን ይችላሉ፡፡ መካድ፣ መውጣት ያሻቸውን የመሆን ነፃነት አላቸው፡፡ በተመስገን አስተሳሰብ ግን ኢህአዴግን ያልተቃወመ ብቻ አይደለም ፣ከእነርሱ ጋር ያልተሰለፈውን ገለልተኛ ሁሉ ኢትዮጵያዊ አይደለም በማለት ይፈርጃል።

ለአመጽ የሚቀሰቅሱት ወጣት በስራ ላይ ነኝ እዛው በጸበላችሁ ሲላቸው ጫታም ፣ ድንጋይ ፈላጭ፣ ጥቃቅን ወዘተ በማለት ሲዘልፉ መንገዳችሁ የጥፋት ነው ብሎ የራሱን አማራጭ በነፃነት ለመጠቀም ያሻውን ፖለቲከኛ ደግሞ ኢትዮጵያዊ አይደለህም ተለጣፊ ነህ ይሉታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ኢህአዴግም የኢትዮጵያውያን ያልሆነ የውጭ ጠላት ነው ብሎ እንደመናገር ሊሆን ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለተመረጠው መንግስት እውቅና፣ ብሎም ለአባል፣ደጋፊ ወይም ተባባሪ ደግሞ ዜግነት የመስጠትና የመንሳት አምባገነናዊ ሥልጣን ከየት እንዳገኘው ባይነግረንም ሃሳቡ ራሱ ኢ-ዴሞክራሲያዊ፣ ሕገወጥና ነውረኛ መሆኑን የማይገነዘብ ገልቱ ቢሆን እንጂ ጀግና የሚሆንበት አንዳች አይነት ተጠየቅ ከቶም ቢሆን የለም፡፡

“የአገር ፍቅር እስከምን ድረስ . . .?” ሲል ተመስገን ጥርቅሙን ይቀጥላል እንደነገርኳችሁ የዜሮ ድምር ነገር ወደነፈሰበትና የማያልቅ በመሆኑ “ኢትዮጵያዊው ማነው?” በሚለው መጣጥፍ የገገርው ፓርቲና የገገርው ፓርቲ ተባባሪ የሆነው ሁሉ ኢትዮጵያዊ አይደሉም ሲል የነበረው ተመስገን “የሀገር

ፍቅር እስከምን ድረስ . . ?" በሚለው መጣጥፉ ደግሞ "ሁላችንንም ሊያስማማ የሚችለው ጉዳይ አገር ከፖለቲካ ልዩነት በላይ መሆኗ ነው" ገጽ 24 በማለት አሁንም ከራሱ ጋር መጋጨቱን ይቀጥላል ፡፡ይህም ይሁንለት እንዳትሉ ደግሞ እዛው በዛው ወደቀደመው የጥላቻ መንገዱ ይሻገራል፡፡

የሀገር ፍቅር በመዋጋት ብቻ እንደማይለካ የሚገልጸው ተመስገን እነሀይሌና አትሌቶቻችን ሩጫ እንጀራቸው ቢሆንም የሚያለቅሱት የሀገር ፍቅር ይዟቸው ነው ፣የሚል ለሀገር ፍቅር መለኪያ እንደማሳያ ያቀርባል፡፡

በመንግስቱ ሃይለማርያም ካራማራ ላይ የተሰቀለውን ባንዲራና በአትሌቶቻችን አቴንስ ላይ የተሰቀለውን ባንዲራ እንደተጨማሪ የኩራት ማሳያነት ያቀረበው ተመስገን ያለምንም ምክንያት "ልዩነቱ ባንዲራው ላይ የኮከብ ምልክት መጨመሩ ብቻ ነው" ገጽ 23 በማለት ያሽሟጥጣል፤

ሀገር ከፖለቲካ ልዩነት በላይ ነው ሲል የተስማማበትን ሃሳብ እርግፍ አድርጎ የተወበትን ጥላቻውንም እዛው በዛው አረጋግጧል፡፡ "ውሃ ቢወቅጡት እንቦጭ"አይነት፡፡

ፌዴራሊዝም ይሄ ከሆነማ" በሚለውና "ኪራይ ሰብሳቢ ስንል...." በሚሉት መጣጥፎችም ቢሆን የተመስገን ጽንፈኝነትና ጫፍ የወጣው ትምክህቱ የተገለጠበት ሲሆን ፍፁም ፀረልማትና ፀረ ህዘብ መሆኑንም የህዳሴው ግድብና ብሄር ብሄረሰቦች ላይ ከሰጠው አስተያየት መረዳት ይቻላል፡፡

በፊት በፊት ተመስገንና መዋቅሩ ሁሉም ነገር ወደትግራይ እየተጓዘ ነው በማለት ሲቀሰቅሱ እንዳልነበር ዛሬ ደግሞ መንገዱ አላዋጣ ሲል ነው መሰል የአክሱም ፣የመቀሌ፣የአደዋ ወዘተ ተቆርቋሪ ሆነው መቅረባቸውን "የትግራይ ህዘብ ማነው?" በሚለው መጣጥፉ ነግሮናል። የመለስ አምልኮን በጨረፍታ ሁለተኛ ክፍል በጥርቅሙ ሁለተኛ ክፍል ዳሰሳ ይቀጥላል፡፡